# ትምህርት አራት

# የአገልግሎት ዓላማ

### ስኬት ከጥሩ ዓላማ የሚገኝ የአገልግሎት ውጤት ነው!

<u>ዓላማ</u>፡- አገልጋዩ አገልግሎቱን የሚፈጽምበትን ዓላማ ጠንቅቆ እንዲረዳና እንዲያገለግል መርዳት።

<u>መግቢያ</u>፤

ለከፉም ይሁን ለመልካም ድርጊት ዓላማ መኖሩ ግልጽ ነው። እርግጥ አንድ እውነት አለ፥ ሰው ሁሉ የሚንቀሳቀስበትን ዓላማ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወይም በንግግሩ ብቻ መረዳት አስቸጋሪ ስለሚሆን፥ ሰው ለምን እንደሚንቀሳቀስ ወይም እንደሚያገለግል የሚለየው በጊዜ ሂደት ነው። ቢሆንም የአገልጋይ ዓላማ ሥጋና አጥንት ያለበት ያህል የተጨበጠ ስለመሆኑ፥ በሕይወቱና በመላ እንቅስቃሴው ሊታይበት ይገባል።

አገልጋዩ የሚኖርበትንም ሆነ የሚያገለግልበትን ምኞትና ዓላማ ለይቶ ማወቅ አለበት። በ1ኛ ቆሮ. 9፡24 መሠረት አገልጋይ ሲያገለግል ዓላማው ግልጽ መሆን ይኖርበታል።

❖ እግዚአብሔርን ሊስበው የሚችለው ጉዳይ መሥዋዕት ማቅረባችን ሳይሆን መሥዋዕቱን የምናቀርብበት (የማቅረብ) ዓላማችን (መነሻ አሳባችን) ነው። ምሳሌ፡- የአቤልና የቃየል መሥዋዕት አቀራረብ ትምህርት ነው (ዘፍ. 4፡1)።

<u>ለምሳሌ</u>፡- አንድ ቦታ የነበሩ የአየር ኃይል ባለሙያዎች ዓላማቸው ምን እንደሆነ ተጠይቀው ሲመልሱ፥ «. . . በዚህ ቅጥር ግቢ ውስጥ ያለነው ሠራተኞች ዓላማችን ተባብረን አውሮፕላኖቻችንን አየር ላይ እንዲሆኑ ማድረግ ነው» ብለዋል ይባላል።

❖ ዛሬስ እኛ ራሳችንን ስንጠይቅ፤ ዓላማችን ምንድን ነው?

ለአገልግሎታችን ዓላማ መሠረት የሚሆኑ አምስት ምክንያቶችን ቀጥሎ እንመለከታለን።

1. የአንድ አገልጋይ ብቸኛና ትልቁ ዓላማ በአገልግሎቱ፡-

   ሀ) እግዚአብሔርን ማክበር ወይም ታላቅ ማድረግ ከዓላማዎች ሁሉ የነጠረ ዓላማ ነው።

ለ) የሚያገለግላቸው ሰዎች እግዚአብሔርን በማክበር ታላቅ እንዲያደርጉት መርዳት ነው።

- ታላቅ አገልጋይ ለመሆን ታላቅ የሆነውን ጌታ በአገልግሎታችን እንደሚገባው ማክበር መቻል አለብን።
- አንድ የእግዚአብሔር ሰው ሲናገሩ «ዓላማችን ታላቅ የመሆን ከሆነ ስሕተት ነው፤ ምናልባትም የተነሣንለት ነገር ለጊዜው ታላቅ ሊያሰኘን ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን ታላቅ ሊያደርገን አይችልም» ብለዋል (1ኛ ቆሮ. 10፡31፤ ሮሜ 15፡9)።
- ስለዚህ የአገልጋይ ታላቅነት የሚወሰነው በሚኖርለት ዓላማ ምንነት ብቻ ነው።

ለምሳሌ፡- የክርስቶስ ትልቁ ዓላማ በአገልግሎቱ አባቱን ማክበር ብቻ እንደነበር፥ በየዘመኑ እርሱም የጠራቸውና የመረጣቸው አገልጋዮች በአገልግሎታቸው እርሱን እንዲያከብሩና ፈለጉን እንዲከተሉ ይፈልጋል (ዮሐ. 17፡4 ይመልከቱ።)

አገልጋይ ጌታው ባስረከበው ማንኛውም ጉዳይ አምላኩን ለማክበር ዓላማ ያለው እንጂ አገልግሎቱን ለራሱ ዝና ማሳያ የመጠቀም ዓላማ ሊታይበት አይገባም። በ1ኛ ሳሙኤል 15፡1–31 የሳኦልን ሁኔታ ስናነሣ እግዚአብሔር የቀባው ሰው ነበር፥ ፍጻሜው ግን ችግር ነበረው። ለምን ብንል ከሾመው እግዚአብሔር ይልቅ የራሱን አሳብ ስላከበረ ነበር። ዓላማን መሳት ማለትም ለእንዲህ ዓይነት ውድቀት ይዳርጋል።

አገልጋይ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሕዝብን ወይም ቤተሰብን ማክበርና ማስቀደም አይገባውም። ምክንያቱም የተጠራው ጌታውን ከሁሉ በላይ ለማክበር ነውና። የእግዚአብሔር ነገር የገባው አገልጋይ ራሱንም ሊያከብር አይሞክርም (1ኛ ሳሙ. 2፡29፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡10–11)። በአገልግሎቱ ጌታውን በማክበር የተመሰከረለት መጥምቁ ዮሐንስ የተናገረውንና የኖረውን ማሰብ ጠቃሚ ነው።

«እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል» ብሏል (ዮሐ. 3፡30)።

አገልጋይ በሚያገለግልበት ዘመን ሁሉ ዓላማዬ ወይም የአገልግሎቴ ግብ ምንድን ነው? መጨረሻ ላይ እንዲሆንልኝ የምፈልገው ምንድን ነው? ብሎ መጠየቅና ለዚያ ጥያቄው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ መጨበጥ ይገባዋል።

ለምሳሌ፡- አንድ የእግዚአብሔር ሰው በአገልግሎት እግዚአብሔርን ስለማክበር ሲናገር «አገልጋይ ሆይ፥ ምናልባት እንኳን ከአገልግሎትህ መሳካት የተነሣ አድናቆት አትርፈህ ሰዎች የክብር አክሊል የሚመስል

ነገር ቢሰጡህ ተቀብለህ በራስህ ላይ ሳይሆን በአገልግሎትህ ባለቤት በጌታ ኢየሱስ እግር ሥር አስቀምጠው» ብሏል። በአጠቃላይ እግዚአብሔርን በአገልግሎታችን የማክበሩን ዓላማ ፈጽሞ መርሳት የለብንም።

2. በአገልግሎታችን ተጠቃሚ የሆኑት ሁሉ አግባብነት ባለው ሕይወት እንዲመላለሱና ክርስቶስን በነገር ሁሉ እንዲያከብሩት ለመርዳት ነው።

«እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው» (ቆላ. 1፡28)።

አገልጋይ ለማገልገል የመመኘቱ ዓላማ በተቀደሰው አገልግሎቱ ሰዎች የተለወጠ ሕይወታቸው የክርስቶስን ሕይወት እንዲመስል ቢሆን በአገልግሎቱ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ማለት ይቻላል። ስኬትም የአገልግሎታችን ጥሩ ዓላማ ውጤት እንደሆነ እኛ አገልጋዮች ማመን አለብን።

<u>ለምሳሌ</u>፤ የፖሊዮን ክትባት ግኝት የተመራመረው ሰው በዚህ በሽታ የሚሠቃዩትን የመርዳትና ይህን በሽታ የማጥፋት ከፍተኛ ፍላጎትና ዓላማ ለመሳካት ትልቅ ጥረት በማድረግ ለ14 ዓመታት በቀን 14 ሰዓታት በሙከራው ምርምር በመትጋቱ ዓላማው ለስኬት እንደበቃ ይነገርለታል። አገልጋይም በአገልግሎቱ ሰዎችን የመርዳት ዓላማ ሲኖረው በአገልግሎቱም ስኬት ይገጥመዋል የሚለው አሳብ እውነትነት ያለው ነው።

3. አማኞች ለእግዚአብሔር ሥራ የተዘጋጁና ጌታን ደስ የሚያሰኝ አገልግሎት እንዲያበረክቱ ለመርዳት ነው።

- ጌታ በአገልግሎቱ ዓላማ ስለነበረው በርካታ ሰዎችን ለመንግሥቱ ሥራ አዘጋጅቷል። ከአገልጋይም የሚጠበቀው እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ነው።

- አገልጋዮችም ለቤተ ክርስቲያንም ብዙ ጸጋ ያላቸው ሰዎች ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። አንዱ ዓላማችን የሰዎችን የማገልገል ጸጋ ማነሣሣት መሆን ስላለበት ማለት ነው።

- አንድ የእግዚአብሔር ሰው እንዲህ ብሏል፤ «የቤተ ክርስቲያን አባላት ስጦታቸውን ከቀበሩ ቤተ ክርስቲያን የቀብር ቦታ ልትሆን ትችላለች»።

- እኛ በአገልግሎታችን ጌታን የማክበርና ደስ የማሰኘት ዓላማ የሚጠበቅብንን ያህል የምናገለግላቸው ሰዎች ወደ አገልግሎት መጥተው ጌታ የሚከብርባቸው እንዲሆኑ መምከር፥ ማስተማር፥ መምራትና ማዘጋጀት ዓላማችን መሆን አለበት (2ኛ ጢሞ. 2፡3 ይመልከቱ።)

4. አማኞች የእግዚአብሔርን ትክክለኛነትና ከፍተኛነት እየተረዱ እንዲያገለግሉ አገልጋዮችን የመርዳት ዓላማን በውስጣችን ሰውረን ማገልገል አለብን።

❖ ዛሬ ብዙ ምእመናንና ጥቂት የማይባሉ አገልጋዮች የአምላካቸውን ማንነት ባለመረዳት ድህነት ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ።

«. . . እስከ እግዚአብሔር ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ» (ኤፌ. 3፡1)።

- ሐዋርያው ለሚያገለግላቸው ሰዎች የሚያልመው (የሚመኘው) ምን እንደነበር እናስብ!

የማገልገላችን ዓላማ የምናገለግለውን ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ፍጹም ሙላት የማድረስና የእግዚአብሔርን ማንነት የማሳወቅ መሆኑን ልብ ማለት ይገባናል።

<u>አገልጋይ</u> በዓላማ በማገልገሉ ውስጥ ምላሾቹ በርካታ ሲሆኑ፥ ከእነዚህ ሁለቱ፡-

❖ በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ምላሽ ይታያል?» (ሉቃስ 7፡28 ይመልከቱ።)

❖ በሰዎችስ ዘንድ ምን ምላሽ ይታያል? (ማር. 6፡14-19ይመልከቱ።)

5. በመጨረሻም የአገልግሎታችን ዓላማ መከሩን መሰብሰብ የሚችሉትን ሠራተኞችን የማፍራት፥ የማሰባሰብና የማዘጋጀት ዓላማ ሊሆን ይገባል (1ኛ ቆሮ. 9፡23፤ ማር. 16፡15 ይመልከቱ።)

«. . . መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት» አላቸው (ማቴ. 9፡38፤ ሮሜ 15፡15)

- የእግዚአብሔር ትልቁ ዓላማ ሰዎችን ማዳን ነው።

- ክርስቶስም ወደዚህ ዓለም የመጣበት ምክንያቱ ይኸው ነበር።

- ለአገልጋይም ከዓላማዎቹ አንዱና ዋነኛው መሆን ያለበት ይኸው ነው። ለወንጌል የመኖር ዓላማ ዋናው ትኩረቱም ለሰው ሁሉ ጠቃሚ በሆነው በወንጌል ላይ መሆን አለበት።

<u>ማጠቃለያ፥</u>

ማንኛውም ሥራ በዓላማ እንደሚሠራና እንዴትም ለውጤት እንደሚበቃ በቀጥታም ቢሆን በተዘዋዋሪ ከትምህርቱ ተረድተናል። የክርስቲያናዊ አገልግሎት ዓላማና ግብ ሁሉን ነገር ለአገልግሎቱ ባለቤት ክብርና ለእርሱ ቤተ ክርስቲያን እድገት እንደሚሆን አስቦና አልሞ መነሣት እንደሚገባ በመጨረሻ ለመጠቆም እወዳለሁ።

# የትምህርት አራት

## የሙከራ (የመወያያ) ጥያቄዎች

«ሙሴም መሠዊያን ሠራ ስሙንም ያህዌህ ንሲ ብሎ ጠራው» (ዘጸ. 17፥15)

1. ዓላማን በሚመለከት ያለህን አጠቃላይ መረዳት ግለጽ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. የአንድ አገልጋይ ብቸኛና ትልቁ ዓላማ በአገልግሎቱ፤

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

3. ዓላማ ለምን ዓይነት ውጤት እንደሚያበቃ አብራራ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

4. የእግዚአብሔር ትልቁ ዓላማ ምን እንደሆነ ግለጽ።

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

5. የወደፊቱ ዓላማህን ግለጽ።

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

# ትምህርት አምስት

# የአገልግሎት ምሳሌ

<u>ዓላማ</u>፡- አገልጋዩ በአገልግሎት ሂደት ውስጥ ምሳሌነት ባለው ሕይወት ማገልገል እጅግ ትኩረት ያለው ጉዳይ መሆኑን ለአገልጋዩ ለማሳየት ነው።

## መግቢያ

አንድ አገልጋይ ለመሆን የሚመኝ ሰው ወደ አገልግሎት ሲመጣና አገልጋይ ሲሆን፥ የሚያገለግላቸው ሰዎች ለእርሱ እንደ አገልጋይነቱ ለየት ያለ እይታ እንደሚኖራቸው፥ ከእርሱ ለየት ያለ ነገር እንደሚጠብቁ፥ ከእርሱ ለየት ያለ ነገር መረዳት እንደሚፈልጉ ማሰብ፥ ማወቅና ማመን ይጠበቅበታል። መጽሐፍ ቅዱስም ምሳሌነት ባለው ሕይወት ማገልገል ከእውነተኛ አገልጋይ የሚጠበቅ ትልቅ ጉዳይ መሆኑን ያስገነዝበናል።

ሐዋርያው ጳውሎስም በመንፈስ ልጁ ለሆነው አገልጋይ ጢሞቴዎስ ከሰጠው ምክርና ማሳሰቢያ አንዱ ለሚያገለግለው ሕዝብ ምሳሌነት ባለው መንገድ አገልግሎቱን እንዲፈጽም ነበር። ወገኖች ቁም ነገሩ ማገልገል መቻላችን ሳይሆን ምሳሌነት ባለው ሁኔታ ውስጥ አልፎ ማገልገል ነው (1ኛ ተሰሎ. 2፡11-12፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡11-12)። በዚህ ቦታ ላይ የጳውሎስ አባባል ምሳሌነት ካጣህ አገልግሎትህ ይናቃል የሚል

ነው። «በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ» (1ኛ ጢሞ. 3፡15)።

ስለሆነም ምክሩ፡-

ሀ) በአነጋገርህ ምሳሌ ሆነህ አገልግል የሚለው የምክሩ መጀመሪያ ሆኖ ይስተዋላል። አንድ አገልጋይ የታረመ ነገር የሚናገር መሆን አለበት ለማለት ነው (ኢዮብ 42፡7 ይመልከቱ።)

- የቀና ንግግር የሚናገር አገልጋይ አገልግሎቱን አክባሪና አስከባሪ እንደሆነም በሌላ ቦታ ሲጠቅስ እናያለን (ቲቶ 2፡7-8)። በንግግራችን ምሳሌነት ማጣት የለብንም (1ኛ ጢሞ. 1፡6፥7)።
- አንተ በእግዚአብሔር ጸጋ ተሞልቶ የሚናገር አገልጋይ ሆነህ ምሳሌ ሁን እንጂ፥ ከሰዎች ጸጋን የሚወስድ ንግግር ከመናገር ተጠበቅ በማለት ማሳሰቡን እንማራለን። «ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ፥ በጨው እንደ ተቀመመ በጸጋ ይሁን» (ቆላ. 4፡6) እንደተባለው ማለት ነው።
- ጸሐፊው ለማሳሰብ የወደደው የአገልጋዩን የንግግር ዘይቤ ሳይሆን፥ የንግግሩን ቅንነት ነው።

❖ አንደበቱን በሚጠብቅ አገልጋይ እግዚአብሔር ይጠቀምበታል፤ ሰዎችም ይታነጹበታል።

ለ) በአኗኗርህ ምሳሌ ሆነህ አገልግል (ማቴ. 23፡3)።

- አንድ እውነት አለ፥ ሰው አውቆና አርሞ መናገር ይችላል፤ ኖሮ መናገር ግን ከባድ ነውና በሰውም በጌታም በኩል የዚህኛው ዋጋ ድንቅ መሆኑን ልብ እያልን በኑሮአችን እንድናገለግል ነው የምክሩ ሌላ ገጽታ።

❖ እኛም አገልጋዮቹ ተገልጋዮቻችንን ከንግግራችን ይልቅ የኑሮአችንን ምሳሌነት እንዲወርሱልን መትጋት አለብን።

- የእግዚአብሔርን ቃል በበቂ ሁኔታ ያወቁና የሚናገሩ፥ ግን ያወቁትንና የተናገሩንት ፈጽሞ መተግበር የማይታይባቸው አገልጋዮች ቁጥር በተበራከተበት በዚህ ጊዜ ጥንቃቄ ልናደርግና ልናገለግል ያስፈልጋል። «ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም፥ ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ።»

❖ በሚደነቅ ርዕስ ካስተማረኝ ይልቅ በሕይወቱ ምሳሌነቱን ያካፈለኝን አደንቃለሁ፤ የማይረሳ ነጥብ ተምሬአለሁ!

«እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል፤» (ማቴ. 5፡19)።

– አገልጋዮች ንግግራችን ታላቅ የሚያደርገን የት ነው?

<u>ምሳሌ</u>፤ ተገልጋዮቻችን እንዲህ ሊሉን ይችላሉ፤ «ስለ ጸሎት 100 ነጥቦችን ካስተማረኝ ይልቅ አብሮኝ በመንበርከክ የጸሎት ሕይወቱን ምሳሌነት ያካፈለኝን አደንቃለሁ፤ ከነጥቦች የሚበልጥ ነጥብ አስተማረኝ።» ይህ አባባል የአገልጋይ ምሳሌነት በተግባር የተደገፈ ሊሆን የሚገባ መሆኑን ያሳያል።

ሐ) በንጽሕና (በቅድስና) ምሳሌ ሆነህ አገልግል (1ኛ ጢሞ. 5፡22)

- አገልጋይ በተበላሸ ነገር ውስጥ ራሱን ቢያስገባ ጸጋውን ያስንቃል! ጸጋውንም ያሰድባል።

- በተለይ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በሌሎች ኃጢአት ጣልቃ ገብ (ተባባሪ) እንዳትሆን ተጠንቀቅ፤ ጸያፍ ነገርን ሁሉ ፍራ፤ ራስህን ረብ የለሽ ከሆነ ነገር ጠብቅ በማለት መክሮታል። ምክንያቱም አንተ እኮ አገልጋይ ነህ የሚል ምክር ለመስጠት መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ምክር ደግሞ በየዘመኑ ወደ አገልግሎት ለምንመጣው ሁሉ ታላቅ ጠቀሜታ ያለው ትምህርት ነው።

መ) በፍቅርህ ምሳሌ ሆነህ አገልግል (ገላ. 6፡1–2፤ ሉቃስ 10፡26)

- ለሰዎች ያለን አክብሮትና በጎ አመለካከት የሚለካው በፍቅራችን ነው።

- ፍቅር ተሞልቶ ወይም ፍቅር እያሳዩ ማገልገል የአገልጋዩ ሕይወት ሊሆን እንደሚገባ ትምህርት ሦስትን ማስታወስ ጥሩ ነው።

- ፍቅር በተሞላ ሕይወት ውስጥ አልፎ በማገልገል ምሳሌነትን ማሳየት ተገቢ ነው።

ሠ) በእምነትህ ምሳሌ ሆነህ አገልግል «. . . ያመንኩትን አውቃለሁና፥ የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ።» (2ኛ ጢሞ. 1፡12)።

- አገልጋይ በእምነት ኖሮ በማገልገል ለሚያገለግላቸው ምሳሌ ይሁን! የሚለው አባባል ታላቅ አባባል ነው። በ1ኛ ጢሞቴዎስ

6፥6 ላይ ያለው ቃል አሳብ ለመቀበል እምነት ወሳኝ መሆኑን ያሳያል። «የታመነም ካህን አስነሣለሁ፥ በልቤም በነፍሴም. . . የታመነ ቤት እሠራለታለሁ» (1ኛ ሳሙኤል 2፥35)።

በመጨረሻም ከላይ ያየናቸውን ምክሮች አቅራቢ የሆነው ጳውሎስ ያወቀውን ብቻ ሳይሆን የኖረበትን ምሳሌነቱን ያስተላለፈልን መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን፤ (ፊልጵ. 3፥17፤ 2ኛ ቆሮ. 11፥1 ይመልከቱ)።

## የክርስቶስ ምሳሌነት በቅዱስ ቃሉ

አገልጋይ የክርስቶስን ምሳሌነት ተከትሎ የማገልገሉ ትልቅ ጠቀሜታ፥ ጌታን እንደሚገባ ያልተረዱ ወገኖች የጌታን ሕይወትና አገልግሎት ነጸብራቅ በማየት ጌታን የበለጠ እንዲረዱና እንዲያገለግሉ ማስቻሉ ነው። የክርስቶስ ምሳሌነት ከሁሉ የተሻለ ምሳሌነት ነው! «. . . እነርሱም እንዲህ አሉት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለነበረው. . . » (ሉቃስ 24፥19)።

## ምሳሌነቶቹን እንመልከት

1. ክርስቶስ ተግባራዊነት በተሞላው መንገድ ሰዎችን ሁሉ እንዳገለገለ፥ አገልጋይም ይህን ምሳሌነት መከተል አለበት። በዮሐ. 13፥12 ላይም «ምሳሌን ተውኩላችሁ» ብሏል።

- ❖ ምሳሌነታችንን ያሳየነው ሁሉ ይከተለናል ለማለት ሳይሆን፥ ኃላፊነታችን በመሆኑ ብቻ እናደርገዋለን። ጫማዎቻችን የሞዴሎች ውጤት የሆኑትን ያህል፥ ምእመናን በምሳሌነት የሚከተሉአቸው የአገልጋዮቻቸው ውጤትም ናቸው።

<u>ለምሳሌ</u>፤ ሙዝን ለማያውቅ ሰው በገለጻ ከማስረዳት ይልቅ ሙዙን ማሳየቱ በቀላሉ እንዲረዳው ያግዘዋል።

አገልጋይነትም በድርጊት የተገለጠ ሲሆን ሰዎች ቶሎ ይረዳሉ፤ አገልግሎቱንም በቀላሉ ሊቀበሉት ይችላሉ። «ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና» (ዕብ. 13፥16)።

አንድ አገልጋይ ሲናገር፥ «ከቀኖቹ ብዙውን ብናስተምርና ተግባራችን ግን አስተማሪ ባይሆን ችግር ነው» ብሏል። ምክንያቱም ሰዎቹ ከእኛ በቂ ነገር አልተማሩም ማለት ይቻላል (1ኛ ጴጥ. 2፥21፤ 1ኛ ዮሐ. 2፥6)።

ሌላው አገልጋይ ደግሞ ማወቅ ያለበት፥ «ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ፈቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን የእኛን በተግባር የተሞላ ሕይወትና አገልግሎት ግን በቀላሉ ለማንበብ ይገደዳሉ።» ይህ ሁሉ ማስገንዘቢያ አገልጋይ በተግባር የተካነ እንዲሆን ስለተፈለገ ነው።

2. ክርስቶስ በርኅራኄ መንፈስ ተሞልቶ ማገልገሉን ከቃሉ የምንረዳው እውነት ነው። አገልጋይም ይህንኑ ምሳሌነት መከተል አለበት (ማቴ. 9፡35፤ ዮሐ. 11፡33-35፤ ማቴ. 14፡14)።

በምሳሌነትም በመጽሐፍ ቅዱስ ምን ዓይነት ሰዎችን እንዳገለገለ ልብ እንበል። ዛሬ ወደ አገልግሎት ለመምጣት የምንመኝ ምን ዓይነቶቹን ሰዎች ለማገልገል ይሆን? ከጌታ ምሳሌነት ምን እንማራለን? ጌታ በርኅራኄ ቀርቦ ካገለገላቸው ጥቂቶቹን ብንመለከት፤

- ወደ ሳምራዊቷ ሴት በርኅራኄ ነበር የተጓዘው (ዮሐ. 4፡1)።
- ለ12 ዓመታት ደም ይፈሳት ለነበረችው ሴት ራራላት. . . (ዮሐ. 5፡25)።
- ለ38 ዓመታት ሽባ ወደነበረው ሰው የመጣው በርኅራኄ ነበር (ዮሐ. 5፡1)።

ጌታ ኢየሱስ በርኅራኄ መንፈስ ለማገልገል ባሰበባቸው ሁኔታዎች ውስጥ የኃጢአተኞች፥ የቀራጮች ወዳጅ የሚል ቅጽል ስም እንደተሰጠው አገልጋይ ልብ ሊለው ይገባል። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት ነገር ሊከሰት እንደሚችል ገብቶት እንዲያገለግል ጠቃሚ ነውና።

- ከላይ ለተመለከትናቸው ዓይነት ሰዎች አገልግሎት ለመስጠት የጌታን ምሳሌነት ከርኅራኄ አኳያ ካልተከተልንና ካላገለገልን በስተቀር አገልግሎታችን ጥያቄ ውስጥ ሊወድቅ ይችላል።

3. ክርስቶስ የሁኔታዎችን እንደተፈለገ ያለመሆን (ችግሮችን) ችሎና ታግሶ ማገልገሉን በመረዳት አገልጋይም ይህን ምሳሌነት በመከተል ማገልገል ይኖርበታል።

«. . . ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ የያዕቆብም የዮሳም የይሁዳም የስምዖንም ወንድም አይደለምን? . . . » (ማር. 6፡3)።

አገልጋይ ነገሮችን እንደየአመጣጣቸው ችሎ ማስተናገድን ከጌታ የሚማረው ትልቅ ትምህርት ነው።

<u>ለምሳሌ</u>፤ ንቀት፡- በኃጢአት የተወለድህ መባሉን፥

- ስድቡን፡- በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል፥ አጋንንታም መባሉን፥

- ጥላቻውን፡- ከአገራችን ውጣልን መባሉንና የመሳሰሉትን ሁሉ እንኳ ቢባል በትዕግሥት ችሎ ማገልገሉ ትልቁ ምሳሌያችን ነው።

❖ ጌታ ሁሉን ታግሦ ተልዕኮውን በመፈጸም አባቱን እንዳከበረ፥ ሰዎችን ሁሉ በተልዕኮው እንዳነጻና እንዳዳነ ወደ አገልግሎት የሚመጣ አገልጋይ ሁሉ ይህን መማር አለበት።

- አገልግሎት ለብዙዎች አልጋ፥ በአልጋ አለመሆኑን አንርሳ።

4. ክርስቶስ አገልግሎቱን በእሺ ባይነት (በመታዘዝ) መንፈስ ማገልገሉን ከቃሉ በመረዳት አገልጋይ ይህን ምሳሌነት መከተል አለበት። የክርስቶስ አገልግሎት ተጀምሮ እስኪፈጸም በመታዘዝ እንደነበርና መታዘዙም ለአባቱና ለሚያገለግላቸውም እንኳ እንደነበር ከቃሉ እንማራለን (ፊልጵ. 2፡8)። አንድ የመቶ አለቃ ልጁን ወደ ቤቱ መጥቶ እንዲፈውስለት ሲጠይቀው ታዞ ሄደ፤ አገለገለ (ሉቃስ 7፡1)።

ዛሬም አገልጋይ ኑ፥ አምጡ ባይ ሳይሆን፥ ታዛዥና አቅሙ በሚፈቅድለት ሁኔታ ውስጥ ሁሉ ሌሎችን በማድመጥ የሚያገለግል መሆን አለበት፤ ጌታ ዝቅ ብሎ ማገልገሉንም ባለመዘንጋት የሚንቀሳቀስና ምሳሌነት ያለው ሊሆን ይገባዋል።

አገልጋይ በማገልገል ብቻ ሳይሆን በመገልገል በሚታዩና በማይታዩ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሁሉ ምሳሌነቱን የማሳየት ነገር ይጠበቅበታል። ለምሳሌ፡- በሕብረት ጥናት ቢሆን በጌታ እራት ቀዳሚ ሆኖ የመገኘት፤ በመስጠትና በመቀበል እንኳ ታማኝነቱን ማንጸባረቅ የሚጠበቅበት የምሳሌነት አደራው ነው።

## ማጠቃለያ

ከዛሬው ትምህርታችን የምንረዳው አገልጋይ የአገልግሎታችን ባለቤት የሆነውን የክርስቶስን ፈለግና የእውነተኛ ቅዱሳን አገልጋዮችን ምሳሌነት በመከተል አገልግሎቱን መፈጸም ያለበት መሆኑን ነው። ስለዚህ ይህን ትምህርት ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ የተረዳነውን ምሳሌነት በአገልግሎታችን ተግባራዊ ማድረግም ይጠበቅብናል።

# የትምህርት አምስት

## የሙከራ (የመወያያ) ጥያቄዎች

«እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» (1ኛ ቆሮ. 11፥1)።

1. አገልጋይ በሕይወቱ ምሳሌነት ቢያጣ ምን ሊሆን እንደሚችል ግለጽ።

2. የአገልጋይ ምሳሌነት ከምን አንጻር ሊሆን እንደሚገባ አብራራ።

3. የክርስቶስን ምሳሌነት በትምህርቱ መሠረት ግለጽ።

4. ስለ ምሳሌነት ያገኘኸውን ትምህርት ግለጽ።

# ትምህርት ስድስት

# የአገልግሎት መሣሪያዎች

<u>ዓላማ</u>፡- ለአገልጋዩ የአገልግሎትን መሣሪያዎች ምንነትና ጠቀሜታ በማሳየት የእነዚህ መንፈሳዊ መሣሪያዎች ተጠቃሚ እንዲሆን ለመርዳት ነው።

## መግቢያ

በዓለማችን ላይ በጣም ትላልቅ ግኝቶች ታይተዋል፤ ይታያሉም። የእነዚህ አስገራሚና አስደናቂ ግኝቶች መንሥዔ የመሣሪያ ጠቀሜታ መሆኑ ግልጽ ነው። ምንም እንኳ አንዱ መሣሪያ ከሌላው መሣሪያ በዓይነትና በጥራት ደረጃ ቢለያይም፥ ማናቸውንም ዓይነት ሥራ ያለመሣሪያ አሳምሮ፥ አቃልሎና አቀላጥፎ መሥራት አልተቻለም፤ አይቻልምም። የሰው እውቀቱ፥ ጉልበቱና ጊዜው ሁሉ በመሣሪያ ሲታገዝ ነው ጥሩና ውጤታማ መሆን የሚችለው። <u>ለምሳሌ</u>፤ በሕክምና ዓለም የተለያዩ እንዳሉ ሁሉ፥ መሣሪያዎች ጠቀሜታቸውም የዚያኑ ያህል በርካታ ነው።

- ❖ ወደ ዋናው አሳባችን ስንመለስ፥ አገልግሎት ትልቅ የጌታ ሥራ ስለሆነ፥ አገልጋዩ ለአገልግሎቱ ጠቃሚ የሆኑትን መሣሪያዎች በትኩረት እየተከታተለ በመጠቀም አገልግሎቱን ከግብ ሊያደርስ መቻሉን ልብ እንላለን። መንፈሳዊው ሥራ ያለመንፈሳዊ መሣሪያ ሊሠራ አይችልምና።

  - መገልገያችንን ሳንገለገልበት የምንሰጠው አገልግሎት ድካም የበዛበት ጥረት ከመሆን አልፎ፥ የመገልገያ መሣሪያዎቹ እንደማያስፈልጉና እንደማይጠቅሙ ማሰብ ይመስላል።

ዛሬም ብዙዎቻችን በጣም የምናውቃቸውና የምናደንቃቸው መሣሪያዎች ብዙ ጊዜ የማናተኩርባቸውና የማንጠቀምባቸው ሲሆኑ፤ ሌሎቹ ደግሞ በእጃችንና በቅርባችን ያሉ ናቸው፤ አሁንም እነርሱን እንመልከታቸው።

ከመሣሪያዎቻችን ዋና ዋናዎቹ

# ክፍል አንድ

## ጸሎት

ለማንኛውም የአገልግሎት እንቅስቃሴ ግንባር ቀደሙና ወሳኙ ጸሎት እንደሆነ አገልጋይ አውቆ በዚህ መሣሪያ ላይ ማተኮር አለበት። ለጸሎት አክብሮትንና ቅድሚያ በመስጠት ለአገልግሎቱ ድጋፍ እንዲሆነውም መከታተል ይገባዋል (ማቴ. 7፡7–11 ይመልከቱ)።

## ጸሎት ምንድን ነው?

1. ጸሎት በእግዚአብሔርና በባሪያዎቹ መካከል ያለውን ኅብረት ማጠናከሪያ የግንኙነት መስመርና የመግባቢያ ቋንቋ ነው። (ዘኁ. 7፡89 ይመልከቱ።)

2. ጸሎት የትላልቅ ለውጦችና በረከቶች ምንጭ መሆኑን ከቅዱስ ቃሉ እናስተውላለን (የሐዋ. 2፡1)። ጸሎት ከእግዚአብሔር የምንፈልገውን የምንቀበልበት ትልቅ መሣሪያ ነው።

3. ጸሎት የፈተናዎቻችንና የአደጋዎች ሁሉ መከላከያና መቋቋሚያ አቅም ነው (ኢሳ. 62፡6፤ 2ኛ ዜና 32፡20)። ይህ ጤናማ የጸሎት ልምምድ ካለን በልዩ ልዩ ችግሮች ተጠቂና ተሸናፊ እንዳንሆን ይረዳናል።

❖ ከአገልግሎቶቻችን ሁሉ ትልቁ አገልግሎት ጸሎት ነው ማለት ስሕተት አይሆንም።

ሀ) አገልጋይ ባለማሰለስና በትክክለኛ ዓላማ ስለሚያገለግለው ኅብረተሰብ መጸለይ የሚጠበቅበት ተግባር ነው። ለምናገለግላቸው ሰዎች ልንጸልይላቸው ኃላፊነት ያለብን መሆኑን ከቃሉ መማር እንችላለን፤ (ኤፌ. 3፡14–19 ይመልከቱ)።

«… የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም. . .» (ቆላ. 1፡9)።

- ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው ሳሙኤል ለሕዝቡ እንዲህ አላቸው፥ «ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ» (1ኛ ሳሙ. 12፡23)። በእግዚአብሔር የተጠራ እውነተኛ አገልጋይ ለሚያገለግለው ሕዝብ የማይጸልይና የማይቃትት ከሆነ፥ በደል እየፈጸመ

መሆኑን ይህ ክፍል ያስገነዝበናል። «ቅጥርን የሚጠግንን፥ ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፥ ነገር ግን አላገኘሁም» (ሕዝ. 22፡30)። እግዚአብሔር የጸሎት ሰው ማጣቱንና ማዘኑን ጠቋሚ አባባል ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን አገልጋይ ሁሌ ከመባከን ተቆጥቦ ለጸሎት ያለውን አክብሮት ለሚያገለግላቸው ማስተማርና በጸሎት ሕይወቱም ማሳየት ይጠበቅበታል። «...ብዙ ሕዝብም ሊሰሙትና ከደዌአቸው ሊፈወሱ ይሰበሰቡ ነበር፤ ነገር ግን እርሱ ወደ ምድረ በዳ ፈቀቅ ብሎ ይጸልይ ነበር» (ሉቃስ 5፡15)።

ለ) አገልጋይ ጸሎት በአገልግሎቱ ውስጥ አዳዲስ ነገሮችን ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያገኝበት እውነተኛ መሣሪያ መሆኑን በመረዳትና ለሁኔታዎች ሁሉ መለወጥ ምክንያት መሆኑን በማመን በቂ ጊዜና አክብሮት ለጸሎት መስጠት አለበት (1ኛ ነገ. 18፡27)።

<u>አገልጋይ</u>፤ እግዚአብሔር የብዙ አዳዲስ ነገሮች ባለቤት መሆኑንና እነዚህ አዳዲስ ነገሮች ወደ ተፈላጊው ቦታና ጊዜ የሚደርሱት በጤናማ የጸሎት ልምምድና ትጋት መሆኑን ልብ ማለት ይጠበቅበታል። አዳዲስ ራእዮችንና መልእክቶችንም በጸሎት ከአምላኩ እጅ በመቀበል ማቀበልም ይችላል።

አንድ ሰው ሲናገር «24 ሰዓት የሚገዳደር ባላጋራ ያለበት አገልጋይ በአንድ ሰዓት ጸሎት ብቻ መርካትና መዝናናት አይገባውም» ብሏል።

- አንዳንዴ አገልጋዮች በልዩ ልዩ እውቀቶች ስንሞላ ጸሎትን ወደ ኋላ የማስቀረት ችግር ውስጥ እንወድቃለንና ጥንቃቄ ያስፈልገናል፤ ይልቁንም ያወቅነው እውነት የእግዚአብሔርን አሳብ ከሆነ አጥብቀን በጸሎት የላቀውን መፈለግ አለብን።

❖ በአገልግሎት ዓለም ሁሌ የሚሮጥና የማይጸልይ አገልጋይ የሚበድል እንጂ የሚሠራ አይደለም!!

- በተለይ ጸሎት በአገልጋዩ ዘንድ አክብሮትን በጣም የሚፈልግ ጉዳይ ነው። አገልጋይ ስለ ጸሎት የሚያውቅ፥ ስለ ጸሎት የተማረና የሚያስተምር፥ የጸሎትን ፕሮግራም የሚያስተባብር ብቻ ሳይሆን፥ ጸሎትን ልምዱ ያደረገ መሆን አለበት (የሐዋ. 6፡1–6፤ ያዕ. 5፡17)። ልምምዱ ሁሌ የተጣደፈም መሆን የለበትም። አገልጋይ መንበርከክ ነው የሚኖርበት። በመንበርከኩ ጠንካራና የተሻለ ነገር ሊወጣው ይችላል (ኢዮብ 39፡1)።

«ኤልያስም እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ፤ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ. . .»

በዓለማችን ከፍተኛ እድገት ከሚታይባቸው ቤተ ክርስቲያናት አገልጋዮች ታሪክ የተማርነው ትልቁ ነገር በአክብሮት የተሞላውን የጸሎት ልምምዳቸውንና የአገልግሎት ፍሬያቸውን ነው። <u>ለምሳሌ</u>፤ የኮሪያዋ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ዴቪድ ያንግ ቹ ስለ ጸሎት ሲናገሩ «የቀኑንና የአገልግሎቴን ብሩህነት የማየው ዓይኔን ስጨፍን (ስጸልይ) እንጂ ዓይኔን ስገልጥ አይደለም» ብለዋል።

- ጸሎት የአስተዋይ አገልጋዮችና በመረዳት ያደጉ ሰዎች ልምምድ መሆኑን ከቅዱስ ቃሉ እንመለከታለን (ዳን. 9፡1–3ን ይመልከቱ።)

ሐ) አገልጋይ በአገልግሎቱ በቤተሰቡና በኑሮው ዙሪያ የሚያንዣብበውን የከፉ ኃይላትን ጉልበት መስበሪያ ብርቱ መሣሪያው ጸሎት መሆኑን አውቆ በጸሎት ባላጋራውን አቅም ማሳጣትና መቋቋም ይኖርበታል (2ኛ ቆሮ. 10፡3፤ ማቴ. 26፡41።)

- አገልጋዩ ሰይጣን አፍኖና አጥሮ የያዘውን የአገልግሎት ክልል በጸሎት ሰብሮ በሰዎች ሕይወት ለውጥ ማምጣት እንደሚችል በጽኑ የተረዳ ሊሆን ይገባዋል፤ ያለዚያ ሁሌ ውጥረት፥ ሰቆቃና ድል መንሣት የሌለበት አገልግሎት ብቻ ይሆናል። አንዱ፡– «ሰይጣን፥ የሚፈራው ሰው ቢኖር በጸሎት ጊዜውን የሚያሳልፈውን ሰው ነው» ብሏል።

- ጸሎት ለአገልጋይ ወደ እግዚአብሔር መጠጊያ፤ ግንኙነት የመፍጠሪያ አንዱ መሣሪያ መሆኑን ሁሌ ልብ ማለት ይገባል።

<u>ጸሎት</u>፡– ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሆነ ምሪት፥

- ❖ ከእግዚአብሔር ለሆነ ራእይ፥
- ❖ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሆነ ድል፥

የሚያበቃን ትልቅ ዕድል ነው (መዝ. 34፡10)።

- ❖ ጸሎት ከሁሉ አስቀድሞ የፈረሰውን አበጅቶ የሚቀርብ መሥዋዕት መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል (1ኛ ነገ. 18፡30፤ ነህ. 4፡14 ይመልከቱ።)

<u>ማጠቃለያ</u>፡– አገልጋይ በግል ሕይወቱም ይሁን በኅብረት ጸሎትን በትልቅ መሣሪያነቱ ሊጠቀምበት የሚገባ ሲሆን፥ ጸሎትን በእኛ ፕሮግራም ውስጥ ሆነን ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፕሮግራም

ውስጥ ሆነን ማድረግ እንደሚገባን፥ ማለትም እግዚአብሔር በሚፈልገው በትክክለኛው መንገድ ላይ ተገኝተን መጸለይ እንዳለብን መዘንጋት የለበትም። (ኢሳ. 59፡1ና 2 ይመልከቱ።)

# ክፍል ሁለት

## የእግዚአብሔር ቃል

<u>መግቢያ</u>፡- አንድ አገልጋይ በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚኖረው ግንኙነት ለሚመግበው መንጋ ትኩስና የበሰለ ነገር ለማቅረብ ያስችለዋል።

አገልጋይ ከእርሱ ቀደም ከነበሩትና በእርሱ ሥር እንኳ ከሚያገለግሉት በትሕትና መማርን የሕይወቱ ልምድ ማድረግ ይኖርበታል። «በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን?. . .» (1ኛ ሳሙ. 15፡22)። የእግዚአብሔርን እውነትና መለኮታዊ አሳቡን ሁሉ የምንረዳው በቃሉ ነው።

አገልጋዩ፥ አዳዲስ ነገሮችን ለመቅሰምና ጥሩ አገልግሎት ለመስጠት በጸሎት መትጋት ብቻ ሳይሆን፥ በንጹሕ ልብ ጌታው የሚናገረውን ለመስማት፥ ለማንበብና ለማገናዘብ ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ቃል ለመጠጋት የተዘጋጀ መንፈስ ሊኖረው የተገባ ነው። «...እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ» (ኢሳ. 48፡17)።

<u>አገልጋዩ</u> የሚገለገልበትን መሣሪያ ጠንቅቆ ከማወቅና ከማሳወቅ አኳያ በቂ ዝግጅት እንደሚያስፈልገው መጽሐፍ ቅዱስ ይጠቁመናል። የአገልጋይ መሣሪያ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በልዩ ልዩ መልኩ (<u>ለምሳሌ</u>፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት፥ በሥልጠና፥ ወዘተ...) መማርና ማወቅ አለበት።

- አገልጋይ በየዕለቱ መሣሪያዎችን እንደሚገባ ከመጠቀሙ አንጻር የጥሞና ጊዜው ወሳኝ ነው።

አገልጋዩ በዚህ የጥሞና ጊዜው እግዚአብሔርን ለመስማት የተዘጋጀ መሆን አለበት። «እግዚአብሔር አምላክ የሚናገረውን እሰማለሁ...፤» [መዝ. (85)፡8]። ሳሙኤልም «ባሪያህ ይሰማልና ተናገር አለ» (1ኛ ሳሙ. 3፡10)።

አገልጋዩ በዚህ የጥሞና ጊዜው እግዚአብሔር ለሕዝቦቹ አስቦ የሚገልጥለትን አውቆና አድምጦ መናገር ከእርሱ የሚጠበቅ ነው። «ሙሴም፦ እግዚአብሔር ስለ እናንተ የሚያዝዘውን እስክሰማ ድረስ ቆዩ አላቸው» (ዘኍ. 9፥8)።

❖ በዚህ የአገልጋዩ የጥሞና ጊዜ የአገልግሎቱ መሣሪያ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በሚከተለው መልኩ መጠቀም ይገባዋል።

1. <u>ቃሉን ማወቅ አለበት</u>። ሠራተኛው ሥራውን የሚያከናውንበትን መሣሪያ አጠቃቀም አውቆ የመጠቀም ታላቅ ኃላፊነት አለበት (ሕዝ. 3፥1–4፤ ቆላስ. 3፥16)። «መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል ስለማታውቁ ትስታላችሁ፤» (ማቴ. 22፥29)። አገልጋዩም መሣሪያውን ለማወቅ በየዕለቱ ከመሣሪያው ጋር የቅርብ ግንኙነት ሊኖረው የተገባ ሲሆን፥ ይህንንም በሚከተለው መልኩ መከታተል አለበት።

አዋቂዎች አገልጋይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚኖረውን ቅርበት በፐርሰንት ሲያስቀምጡት፥ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት 50% ፥ በማንበብ 60% ፥ በማጥናት 80% ፥ በማስታወስ 90% ፥ የእግዚአብሔርን ቃል በማሰላሰል 100% ። በዚህ መሠረት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ጊዜ ከሰወድን በመሣሪያችን ጥሩ ተጠቃሚና ጠቃሚ መሆን እንችላለን። «ቃልህ እጅግ የነጠረ ነው፥ ባሪያህም ወደደው» [መዝ. (119)፥140]።

አገልጋዩ ስለሚገለገልበት መሣሪያ በቂ እውቀት ሊኖረው ይገባል፤ ይህ የሚሆነውም ያማያቋርጥ ተማሪ በመሆን ነው (ኢያሱ 1፥7–9)። እዚህ ላይ አገልጋይ በግል ከመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ተምሬአለሁ፤ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎችን ወስጃለሁ ብሎ ስንፍናን በውስጡ እንዳያሳድግ ማሰብ ይገባዋል። በእርግጥ ከልዩ ልዩ ሥልጠናዎችና ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶቻችን ብዙ ጥቅሞችን ልናገኝ እንደምንችል ጥርጥር የለውም፤ ነገር ግን እነዚህ መንገዶች እንዴት እንደምንሰማ፥ እንደምናነብ፥ እንደምናጠና፥ ወዘተ... ያሳዩናል እንጂ ከዚያ ያለፈውን ሊያደርጉልን አይችሉም።

❖ የጥሞና ጊዜያችን ግን ከሁሉ የላቀውን መሣሪያችንን በጣም ሊያስተዋውቀን የሚችል ትልቅ መንገድ ነው።

<u>ለምሳሌ</u>፥ ስለ ምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ መማር (ማወቅ) ማለት መመገብ ማለት እንዳልሆነ ሁሉ፥ እንደዚሁ በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶች መማር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያሳውቀናል እንጂ የቃሉን ሙላትና ኃይል እስከ መጨረሻው ይሰጠናል ማለት አይሆንም።

የጥሞና ጊዜያችን ግን መጽሐፍ ቅዱሳችንን በተሻለ መልክ ያሳውቀናል ማለት ስሕተት አይመስለኝም።

- ስለዚህ አገልጋይ የአገልግሎቱ መሣሪያ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ለሚያጠናበት ለጥሞና ጊዜው ትልቅ ትኩረት መስጠት አለበት።

❖ በክርስትና ሕይወታችን እድገትን መጠበቅ የሚኖርብን መንፈሳዊ ጥማትና ረሃብ በውስጣችን እስከተሰማን ድረስ ብቻ ነው።

- መራብና መጠማት የጤንነት ምልክትም ነው።

- «ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥ ይጠግባሉና፤» (ማቴ. 5፡6)።

2. ቃሉን ማመን አለበት፤ ማንኛውም ሠራተኛ ሥራውን በሚያከናውንበት መሣሪያ አጥብቆ የሚተማመን መሆን አለበት።

አገልጋዩ በእግዚአብሔር ቃል ኃይል፥ ታላቅነት፥ ፈዋሽነት፥ ተስፋ አዳሽነት፥ ወዘተ... መተማመን ይኖርበታል። ያላመኑበትን ማውራትም ችግር ነው። ስለሆነም አገልጋይ በማያውቀውና ባልለመደው መሣሪያ መጠቀም ወይም መገልገል የለበትም። «ዳዊትም ሳኦልን፦ አልፈተንሁትምና እንዲህ ብዬ መሄድ አልችልም አለው» (1ኛ ሳሙ. 17፡39)።

በሐዋርያት ሥራ ላይ የአስቄዋ ልጆች ባላወቁትና ባላመኑበት መሣሪያ ስለተጠቀሙ ጉዳት ገጠማቸው እንጂ አልተሳካላቸውም። በሰው መሣሪያ (ትጥቅ) መዋጋት አደጋ አለው (የሐዋ. 19፡13–16)። ከሌላው ሰምቶና አይቶ ማገልገልን መልመድ አንድ ወቅት ላይ ለችግር ያጋልጣል። ከሌላው የተረዱትን ለራስና ለሌላው ጥቅም ማዋል ከፋት ባይኖረውም፥ ሁሌ የኩረጃን ሕይወት መለማመድ ግን መሳት ነው።

3. ቃሉን ማክበር (መታዘዝ) አለበት (ማቴ. 7፡24)

አገልጋይ የእግዚአብሔርን ቃል ከራሱ ልምምድ፥ ስሜትና ፈቃድ በላይ በማክበር ለሰማውና ለተረዳው እውነት በመታዘዝ ሕይወቱን ማስለመድ፥ ሁኔታዎችን ሁሉ በቃሉ መመዘንና ቃሉን ከፍ አድርጎ ማግነን ይጠበቅበታል።

አገልጋይ፥ ለተረዳው የእግዚአብሔር ቃል ታዛዥና ተገዢ በመሆን፥ ለሚያገለግላቸው ሰዎች በሕይወቱ ጥሩ አስተማሪ መሆን ይገባዋል።

አገልጋይ የእግዚአብሔርን ቃል አውቆና አጥርቶ በመረዳት እስከ ፍጻሜው በቃሉ መሄድ አለበት፤ (1ኛ ነገ. 13፡1)።

4. ቃሉን ማስተማር (ማስተላለፍ) አለበት። የተጠቀሙበትን ለሌላው ጥቅም ማዋል!

በአገልጋይ ዙሪያ በመሣሪያው በመጠቀምና ባለመጠቀም ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። «በዚያም ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበረ፤ ራእይም አይገለጥም ነበር» (1ኛ ሳሙ. 3፡1)። «...የጌታም ባሪያ ለሰው ሁሉ ገር ለማስተማርም የሚበቃ . . . » (2ኛ ጢሞ. 2–24) መሆን እንዳለበት እንማራለን።

የጌታ ባሪያ ያመነውን ማሳመን፥ ያወቀውን ማሳወቅና ያከበረውን ማስከበር አደራውም ስለሆነ፥ አገልጋይ የተላለፈለትን የማስተላለፍ ኃላፊነት አለበት። ይህንንም ስንል አገልጋይ ማሰብ የሚኖርበት በብዙም ይሁን በጥቂት ጉባኤዎች ቃሉን ለማስተማርና ለመትጋት እንጂ፥ የግድ የተከማቸን የሕዝብ ብዛትና ትላልቅ መድረኮችን በመጠበቅ ዘመኑን፥ ጊዜውን ማባከን እንደሌለበት ነው። ለምሳሌ ያህል የአቂላና ጵርስቅላን አገልግሎት ማሰብ ይቻላል።

አገልጋይ አደራን በመዘንጋት የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቆ አለመያዝ የሚያስከትለውን ችግር ማወቅ አለበት። «ዕዝራም የእግዚአብሔርን ሕግ ይፈልግና ያደርግ ዘንድ፥ ለእስራኤልም ሥርዓትንና ፍርድን ያስተምር ዘንድ ልቡን አዘጋጅቶ ነበር» (ዕዝራ 7፡10)።

ማስታወሻ

- መሣሪያውን የማወቅና የመጠቀም ፋይዳ ምንድን ነው?

ሀ) አገልጋዩን በአገልግሎቱ ዙሪያ በአዳዲስና በጊዜው መልእክት ለመሞላት መርዳቱ ነው።

- ትኩስ ነገር መመገብ የአገልጋዩ ኃላፊነት በመሆኑ፥
- ለመንጋው በቂ ምግብ ለማቅረብ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መጠጋት ጠቀሜታ ስላለው፥
- ታማኝ ሆኖ የተመገበ ታማኝ ሆኖ መንጋውን ለመመገብ ስለሚችል ነው።

«እስከመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ» (1ኛ ጢሞ. 4፡13)። መንጋውን በቀናና በትክክለኛ መንገድ ለመምራት መርዳቱ ነው (ሕዝቅ. 33፡7–9)።

ለ) የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ከሌሎች መጻሕፍት ሥልጣን የላቀ መሆኑን በሚገባ ለማሳየት የሚረዳ በመሆኑ።

- ❖ እግዚአብሔር ራሱን ከሚገልጥባቸው መንገዶች ትልቁ በቅዱስ ቃሉ አማካኝነት ነው።
  - በመንጋው ሕይወት የሚያቅበዘብዝ ፍልሰትን ለመቋቋምና ከሚያስቱ ነጣቂዎች ለመጠበቅ ስለሚረዳ ነው።
- ❖ በመንጋው ሕይወት መንፈሳዊ ስደተኝነትን የሚያስነሣው መንፈሳዊ ረሃብና ጥማት ስለሆነ፥ አገልጋይ በበቂ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ድምጽ በመስማት ከበለጸገ ችግሩን ያጠፋል ባይባልም እንኳ መቋቋም ይችላል።

ማጠቃለያ፥ ስለዚህ አገልጋይ ሁልጊዜ የጥሞና ጊዜውን በማክበርና በማጠናከር የአገልግሎቱ ሌላ መሣሪያ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል በመጠቀም ሕይወቱንና አገልግሎቱን መጠበቅና መንከባከብ እንደሚችል ማመንና በዚያም ማተኮሩን ማሰብ አለበት።

# ክፍል ሦስት

# መንፈስ ቅዱስ

መግቢያ፡- ለአገልጋይ መጸለዩና የእግዚአብሔርን ቃል መጠቀሙ ለብዙ ስኬት እንደሚያበቃው የተረዳን መሆኑ እንደተጠበቀ ቢሆንም፥ ለእነዚህም መሣሪያዎቻችን አጠቃቀም እንኳ በቂ ችሎታና ጥበብ፥ ኃይልም ልናገኝበት የምንችለው በሌላው ትልቅ መሣሪያችን አማካይነት ነው። እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ዙሪያ የተለያዩ አመለካከቶች መኖራቸው የታወቀ ሲሆን፥ አገልጋይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆኑት እውነቶች ላይ በማተኮር በመንፈስ ቅዱስ ሁሌ ለመሞላትና ለመመራት ፍጹም ዝግጁ መሆን አለበት።

መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና ጌታ ኢየሱስ ለአገልጋዮቹ በሰጠው ማሳሰቢያ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ሳይቀበሉ ለአገልግሎት መውጣት እንደማይገባ መናገሩ የሚታወስ ነው።

«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ...» (የሐዋ. 1፡8)።

አገልጋዩ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመሥራት ሥራውን ሊያቀናለት እንደሚችል ልብ ማለት አለበት (ሕዝ. 37፡1፤ የሐዋ. 10፡38)።

- መንፈስ ቅዱስ ለአገልጋዩ የራእይ፥ የድፍረት፥ የብቃትና የስኬቱም ምንጭ እንደሆነ ማሰብና ሁሌ በእርሱ ተደግፎ መሥራት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው (ራእይ 1፡10)። መንፈስ ቅዱስ በውስጥ የደነዘዘውንና በውጭ የታወረውን የሚለውጥ ኃይል ነው። «. . . በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም» (ዘካ. 4፡6)።
- በአገልግሎታችን ውስጥ ኃጢአትን ከጽድቅ መለየት የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው (የሐዋ. 5፡1)። አንዳንዴ በስውር የቤተ ክርስቲያንን የአገልግሎት ሂደት ሊያበላሹ የሚሽሎከሎኩትን መግለጥ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።

- መንፈስ ቅዱስ ለአገልጋዮቹ የተሰጠ ተስፋ ነው።

<u>ተስፋው፡-</u>

ሀ) ከዘመናት በፊት በነቢያት የተነገረ ነበር (ኢዩ.2፡29፤ ሕዝ. 36፡25-27፤ ኢሳ. 44፡3-4)።

ለ) ክርስቶስም መስክሮ ያጸናው ተስፋ ነበር (ዮሐ. 14፡15-17፤ ሉቃስ 24፡49፤ የሐዋ. 11፡16፤ 1፡8)።

ሐ) በትክክልም የተፈጸመና ወደፊትም ጌታ እስኪመጣ ሲፈጸም የሚኖር ተስፋ ነው (የሐዋ. 2፡1-4፤ 4፡31)።

<u>ተስፋው፡-</u>

1. ለአይሁድ (የሐዋ. 2፡1) ትልቅ ሥራ የተሠራበት በዓል ነበር፤ ለምሳሌ፥ የበዓለ ኀምሳ በዓል
2. ለሳምራውያን (ለክልሶቹ) ነበር (የሐዋ. 8፡15-18፤ 19፡1-7)።
3. ለአሕዛብ (ለአረማውያን) ነበር (የሐዋ. 10፡44-46)።
4. ለሁሉም የተሰጠ ነበር (ማር. 16፡17)።

- ❖ አገልጋይ ይህን እውነት በመረዳት ለመንፈስ ቅዱስ ተገቢውን ስፍራ በመስጠት መንፈሳዊ ስጦታና መንፈሳዊ ፍሬም የሚታይበት ሊሆን ይገባል።

የመንፈስ ቅዱስን ሁለት መሠረታዊ ተግባራት ማወቅና መከተልን አገልጋይ ሁሌ ማስታወስ አለበት።

1. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሮሜ 12፡6–8 እና በ1ኛ ቆሮ. 12፡4 ይመልከቱ። ይህ አገልጋዮች ሁልጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውስጥ ስንገኝ ጌታ በሕይወታችን የሚገልጠው ጠቃሚ ስጦታ ከሆኑት አንዱ ነው።

   - አገልጋይ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሲነግ መዘንጋት የማይኖርበት የስጦታውን ዓላማ ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡7)

በሁሉም ክርስቲያን ዘንድ መታወቅ ያለበት ትልቅ ጉዳይ ደግሞ ስጦታዎች ስጦታ መሆናቸው እንጂ ሙያ አለመሆናቸው ነው። <u>ለምሳሌ፥</u> የዓይን ሕክምና ዶ/ር ሁሌ በሥራ ገበታው ተገኝቶ ሕሙማኑን ሊረዳ (ሊያክም) ይችላል። ሁሌ ይህን እንዲያደርግ ሙያው ያስገድደዋል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ግን እንዲህ ያለመሆኑን ከቃሉ እንማራለን (2ኛ ጢሞ. 4፡20)። ጥሮፊሞስን ታሞ ተውኩት (1ኛ ጢሞ. 5፡23)፤ ጢሞቴዎስን የወይን ጠጅ ጠጣ ብሎ ብቻ መከረው።

ከእነዚህ ጥቅሶች የምንማረው አገልጋይ እግዚአብሔር በሚሰጠው የጸጋ ስጦታ ሰዎችን የሚያገለግል ቢሆንም፥ የእግዚአብሔር መጠቀሚያ እንደመሆኑ መጠን፤ እግዚአብሔር ሲያናግረው የመናገር፥ ዝም ሲያሰኘው ዝም የሚል፤ የሚገልጥለትን የሚገልጥ፥ የሰወረበትን ከእኔ ሰውሮታል የሚል መሆኑንም ነው።

አገልጋይ እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ ያስቀመጠውንና በሌሎች ውስጥ ያስቀመጠውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንዳይዳፈን ማነሣሣት (ምእመናንን ማደፋፈር) አለበት። ነገሩ ሁሉ ግን እንደ ቃሉ መሆኑንም መፈተሽ ይገባል።

2. የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ (በገላትያ 5፡22 ይመልከቱ።)

❖ ቤተ ክርስቲያንም የምትታነጸው መንፈስ ቅዱስ በውስጧ በሠራና የመንፈስ ፍሬዎችም በተገለጡባት መጠን ነው።

❖ ሌላው መንፈሳዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ መልካም ልምምዶቻችንን በቅንነት እየጠበቅን በመንፈሳዊ ፍሬ አጅበን ልንጠቀምባቸው ይገባል።

- አገልጋይ ለመንፈስ ቅዱስ አሠራር ትልቅ ስፍራ በመስጠት፥ በእርሱ በመጠቀምና ልቡን በመክፈት አገልግሎቱን ካላስረከበና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መንቀሳቀስ ካልቻለ፥ ታሪኮችን አሳምሮ

ከመናገር ያለፈ ለውጥ በሕይወቱና በሚያገለግላቸው ሰዎች ሕይወት ዙሪያ ማምጣት ይከብደዋል። ሠርቶ ከሚያሠራው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መሥራት የሥራውን አጨራረስ ያሳምረዋል!

❖ መንፈስ ቅዱስ ከመሣሪያዎች ሁሉ የተሻለና የሌሎቹንም መሣሪያዎች ውጤት የሚያረጋግጥ እንደሆነ ይታመናል። ለምሳሌ፥ መዶሻ ምስማርን ለመምታት ጥሩ መሣሪያ ነው፤ የመዶሻው ተጠቃሚ ደግሞ በጣም የተሻለ ነው።

ውጤት ባለውና ጥሩ አጨራረስ በሰፈነበት ሁኔታ አገልግሎትን ለመፈጸም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መውጣት በጣም አስፈላጊ ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተቀቡ አገልጋዮች አገልግሎታቸው ታላቅ መነቃቃትን ያመጣል። እንዲህም ስንል በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉና የተመሩ፥ እርሱን የሚደግፉ ለማለት ነው (1ኛ ተሰሎ. 1፡5)።

- በተጨማሪ ለአገልጋይ ጥሩ መሣሪያ ናቸው ከሚባሉት መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-

1. ታማኝነት (1ኛ ቆሮ. 4፡2፤ ዕብ. 3፡5፥6)።
2. ትጋትና ንቃት (ምሳሌ 12፡24፤ 1ኛ ቆሮ. 16፡13፤ ምሳሌ 21፡5)።
3. ትዕግሥትና ጽናት (1ኛ ቆሮ. 15፡58፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡25፤ ያዕ. 5፡8፥10)።
4. ትሕትና (ማቴ. 11፡28)፤ ትሕትና ከሸክም የተነሣ የሚመጣ ነው።

ለጊዜው እነዚህን የአገልጋዩ መሣሪያ ናቸው ብለን ለማለፍ ብንገደድም፥ በጣም ጠቃሚና ዋና ዋና ከሚባሉት መሣሪያዎች ጋር የሚመደቡ መሆናቸውን ግን አጥብቄ ሳልጠቁም አላልፍም።

## ማጠቃለያ

እነዚህ ከላይ ያየናቸው መጠነኛ የአገልጋይ መሣሪያዎች በጸሎት መትጋትን፥ ከቃሉ ድምጹን መስማትን፥ በመንፈስ ቅዱስ መደገፍንና ሌሎችንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነጥቦች ያካትታሉ። እነርሱንም በመንፈሳችን ስፍራ በምንሰጣቸው እውነቶች ተጠቅመን ፍሬ ወዳለው አገልግሎት መድረስና አገልግሎታችንን በቀላሉ ማከናወን እንደምንችል ለጥቆማ ያህል ተመልክተናልና በሕይወታችን ስፍራ እንስጣቸው።

# የትምህርት ስድስት

## የሙከራ (የመወያያ) ጥያቄዎች

«በወንጌልም ማኅበርተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ» (1ኛ ቆሮ. 9፡23)።

1. ማንኛውም ሥራ ያለመሣሪያ እንደማይሠራ ግልጽ ነው። የአገልግሎት መሣሪያ ናቸው የምትላቸውን አብራራ።

2. ጸሎት ለአገልግሎትህ እንዴት መሣሪያ ሊሆን እንደሚችል ግለጽ።

3. የእግዚአብሔር ቃል ለአገልግሎትህ እንዴት መሣሪያ ሊሆን እንደሚችል አብራራ።

4. መንፈስ ቅዱስ ለአገልግሎትህ በመሣሪያነቱ ያለውን ጠቀሜታ ግለጽ።